# ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፐረስ 1/8/2021:  የመልሶ መከፈት ውሳኔ ወቅታዊ መረጃ በየሳምንቱ ሰኞ እለት ይቀርባል

**የዚህ ሳምንት ዋና ርእሶች**


- የመልሶ መከፈት ውሳኔ ወቅታዊ መረጃ በየሳምንቱ ሰኞ እለት ይቀርባል።
- የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ውጤቶች
- በካፒቶል እርብ ቀን ስለተከሰተው ሁኔታ ከልጆችዋ ጋር ለማውራት የሚያግዙ ድጋፍ ሰጪ ነገሮች ሪሶዋርሶች
- የተለመዱ የክትባት ማስታወሻዋች
- አዲስ ዙር በወረርሽኝ ምክንያት የሚሰጡ  ኤሌክትሮኒክ የገንዘብ  ድጋፍ አሰጣጥ በቅርብ ይጀመራል
- የቴ.ሲ  እና  የማውሪ አዲስ ስም ስያሜ ለተማሪዎች የመጨረሻ እድል
- የትምህርት ቤት ቦርድ   Alderton  በ2021 በሊቀመንበርነት ለመሾም ውሳኔ ሰጠ።
- ሱፐር ኢንቴንደንት የጥምር ፈንድ የስራ ማስኬጃ በጀት ለመልሶ ግንባታ፣ የማቆየትና የማጥናከር ስራ የሚያግዝ በጀት  ራቂቅ አቀረቡ።
- ቦርዱ ተገቢ ኋላፊነት የሚያሳይ የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት አፀደቀ።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.  የተቆማት አደረጃጀትና አመራር አዲስ ስራ እስፈፃሚ ሾመ።
- የምግብ አቅርቦት


---

የተከበራችሁ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባላት፤

በቅድሚያ ወደ የርቀት ( ቨርችዋል) ትምህርት እንኳን በደህና ተመለሳችሁ እላለሁ። እናም ለሁላችሁም አዲሱ 2021 የጤና እና የደስታ ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ።  ይህን ለየት ያለ የበዓል ወቅት መልካም ግዜ እንዳሳላፋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ እንዲሁም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ጥሩ ግዜ  በቅርብ እና በሩቅም ካሉት ጋር እንዳሳሳፋችሁ እገምታላሁ በአካል ተገናኝቶ ባይሆንም እንኳን።

ስለክትባት ፕሮግራም በየግዜው የሚሰራጨውን መረጃ በመመለከት የ2021 ተስፋ ያለው ይመስላል።  የK-12 ሰራተኞች ክትባቱን ለማግኘት ተራ እንደሚያገኙ በደረጃ I (Phase 1b)  የቨርጅኒያ የጤና ዲፓርትሜንት የኮቪድ ክትባት ፕሮግራም እቅድ  በዚህ ሳምንት ተረድተናል።  ስለክትባቱ ለሰራተኞች እና ተማሪዎች መገኘት የምናገኘውን ወቅታዊ መረጃ  ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት መረጃው እንዳገኘን በየግዜው እናቀርባለን ።  ይህ በእንዲህ እንዳለ የከተማው የጤና ሁኔታ መመዘኛ መስፈርቶችን በቅርበት ክትትል እንዳርጋለን እና ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት  ጋር በየቀኑ ግንኙነት እንዳርጋለን።  የእኛ ከተማ እና ስቴት የወረርሽኙ ሁኔታ በየግዜው እያደገ ይታያል።  ሰኞ፣ ጃንዋሪ 11 ቀን በከተማአቀፍ ፕሮግራም የመጀመሪያ ዙር ተማሪዎች ወደ ት/ቤት በጃንዋሪ 19 ቀን የሚመለሱ ተማሪዎችን በተመለከተ  የሚሰጠውን ውሳኔ ወቅታዊ መረጃ እናቀርባለን።  በየሳምንቱ ሰኞ ያጋጠሙንን ነገሮች  በውሳኔ መስጫ መስፈርቶች መሰረት የኮሚዩኒቲ ጤንነት ሁኔታ ፣ የስራተኞች እና ያለንን አቅም በማገናዘብ ግምገማ ይደረጋል።   የተማሪዋችና ሰራተኞች  ደረጃ በደረጃ ወደ ት/ቤት የመመለሱ አሰራር በተመለከተ ለውጥ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ይፋ ይደረጋሉ።

በክረምቱ ወቅት ስራችንን በጥንካሬ ስናከናውን የቆየን ሲሆን ወደ ድብልቅ የትምህርት አሰጣጥ ለመቀየር ዝግጅት ስናደርግ ቆይተናል። የግዜ ሰሌዳዎች ተዘጋጅተዋል እና  ኮሚዩኒቲው የእኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ምን እንደሚመስል እንዲረዳው ለማስቻል የመልሶ መከፈት የሚያስችሉ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል።  የእኛ ውሳኔ መስፈርቶች ለሳምንታዊ ወቅታዊ መረጃ እቅርቦት በተጨማሪ  ቤተሰቦችን በድብልቅ የትምህርት አሰጣጥ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ የልጅዎ የድብልቅ የግዜ ሰሌዳ ፕሮግራሙ ከመጀመሩ ሁለት ሳምንት አስቀድሞ እንዲደርሳች ይደረጋል።  የድብልቅ የግዜ ሰሌዳ በተጨማሪ የልጅዎ አስተማሪ ወደ ት/ቤት ተመልሶ ለመስራት ፍላጎት ያሳየ ስለመሆኑ ወይም በቨርችዋል ብቻ እንደሚያስተምር በተጨማሪ ይገለፃል።  በዚያ ደረጃ ወቅት ቢፓወር ስኩል የድብልቅ ፕሮግራም ለመረጡ ቤተሰቦች የድብልቅ ፕሮግራም  በአስተማሪው በአካል በመገኘት / በቨርችዋል ብቻ የሚያስተምር መሆኑ ጋር በተያያዘ፣ የኮሚዩኒቲ

ጤንነት መስፈርት፣ ክትባት በወቅቱ መገኘት እና /ወይም በዩ.ኤስ. አዲስ የቫይረሱ ዓይነት ስርጭት ጋር በየተያያዘ የቤተሰብ ውሳኔ የሚለወጥ ከሆነ ወቅታዊ ውሳኔ እንዲያሳውቁ ለማስቻል የቤተሰብ ምርጫ ቅፁን መልሰን እንጀምራለን።

በዚህ የሽግግር ወቅት እንደሚያውቁት የእኛ ሰራተኞችና ተማሪዎችን ጤንነት መጠበቅ ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ይህም ቤተሰቦችና የሰራተኞች ፍላጎት የመጠበቅ በጣም የፈጠራ አሰራርን ይጠይቃል። የተወሳሰብ ስራ ነው ሆኖም ግን እኛ ሰራተኞችና የተማሪዎቻችን ጤንነት በአንድ ላይ መጠበቅ እንችላለን። በብቃት ለመስራት ለመቻል ተለዋዋጭነት እና በዚህ ሰዓት ከወረርሽኙ በፊት የነበረውን የትምህርት አሰራር መከተል እንደማንችል ይታወቃል። ሆኖም ግን ምርጥ የሆነ የትምህርት ልምድ ለተማሪዎቻችን በድብልቅ የትምህርት አቀራረብ እና በርቀት (ቨርችዋል) ማቅረብ እንደምንችል እምነት አለን ። የተማሪዎቻችን ማህበራዊ ፣ ስሜት እና የአካዳሚ ፍላጎት ማሟላት በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

የ2021 ጉዞችንን ስንጀምር ትብብር፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ እንቀጥላለን እንዱሁም ይህን ያልተለመደ ጉዞ ስንጀምር መረጃ ልውውጥ ይቀጥላል። የኮሚዩኒቲ ስርጭቱን በአሌክሳንደሪያ እና ከዚያም ውጭ ለመቀነስ ጤንነትዋን ይጠብቁ፣ የማህበራዊ ርቀት ይጠብቁ።

Gregory C. Hutchings, Jr.
የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት (ዋና ስራ አስኪያጅ)

## ት/ቤት መልሶ መከፈት ውሳኔ ወቅታዊ መረጃ በየሳምንቱ ሰኞ እለት ይቀርባል

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እና የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት (AHD) የመልሶ መከፈት ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ሶስት መስፈርቶችን በአንድ ቻርት አዘጋጅተዋል ፤ የኮሚዩኒቲ ስርጭት መጠን፣ በበሽታው መያዝ መረጃ፣ እና በትምህርት ቤቶች ላይ የሚኖረው ተፅእኖ ያካትታል። ዓላማው መስፈት በማዘጋጀት ቤተሰቦች በየደረጃው ወደ ት/ቤት ለመመለስ የሚደረገውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲረዱት ማድረግ ነው።

መስፈርቱ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ድረገፅ ላይ ይወጣል እና በየሳምንቱ ሰኞ ወቃታዊ አዲስ መረጃ እንዲወጣ ይደረጋል። በመስፈርቱ ያሉ መረጃዎችን በመጠቀም በየሳምንቱ ሰኞ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ወቅታዊ መረጃዎችን በድረገፁ ላይ እንዲወጣ ያደርጋል። መረጃዎቹ በተጨማሪ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ አማካኝነት በእሮብ መደበኛ እትም ላይ እንዲወጣ ይደረጋል።

View the Reopening Decision Matrix.

Video: Learn how the Reopening Decision Matrix works:




የተማሪዎቻችን ወደ ት/ቤት የመመለሻ ግዜ ሰሌዳ በጃንዋሪ 19 ቀን ( ለት/ቤት ቦርዱ በቀረበው የግዜ ሰሌዳ መሰረት ) የሚወሰነው በኮሚዩኒቲው የጤና መስፈርት መሰረት፣ የሰራተኞች እና የአቅም ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው። i

## የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ጥያቄዎች

የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ጥያቄዎች ከክረምት እረፍት ግዜ በፊት ምላሽ ለሰጡ ቤተሰቦች ምስጋና አናቀርባለን ። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የ83% ምላሽ አግንቶል። ይኸም የ12,000 ተማሪዎች ቤተሰቦች ግዚያቸውን ወስደው ቅፁን በፓወር ስኩል የወላጆች መግቢያ ሞልተዋል።

በአጠቃላይ 59.5% የሚሆኑ የተማሪዎች ቤተሰቦች በርቀት (ቨርችዋል) የትምህርት አሰጣጥ (ይህም 17% መልስ ያልሰጡ ቤተሰቦችን በመሆኑም ቨርችዋል እንደመረጡ የተቆጠሩትን ይጨምራል) ለመቀጠል መርጠዋል ።

ልዩነት ተንፀባርቆል በዘር/ብሔረሰብ ሲታይ፤ 53% የሚሆኑ ነጭ ተማሪዎች፣ 42% የስፓኒሽ ተማሪዎች እና 27% ጥቁር ተማሪዎች የድብልቅ ትምህርቱን መርጠዋል። በተጨማሪም በክፍል ደረጃ ሲታይ ከፍ ያለ ቁጥር የድብልቅ ትምህርት የተመረጠው በህፃናት ተማሪዎች እንደሆነ ልዩነት ተንፀባርቆል። በትምህርት ቤት በኩልም ሰፋ ልዩነት ታይቶል ፤ 68% የጆርጅ ሜሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የድብልቅ ትምህርት መርጠዋል ከ26% የፓትሪክ ሔንሪ ት/ቤት ጋር ሲነፃፀር።

በርካታ ጉዳዩች ምክንያቶች እንደሉ እናውቃለን - ክፍ ያለ የኮሚዩኒቲ መስፈርት መኖር፣ የክትባት የግዜ ሰሌዳ ፤ አዲስ የቫይረሱ ዓይነት መታየት - መኖር ምርጫዎ ከዲሴምበር በኋላ ሊቀየር ይችላል። እባክዎን የሚኖሩት አማራጮች በሚመመለከት በቤተሰብ ምርጫ ቅፅ በመጪዋቹ ሳምንታት ወቃታዊ ለማድረግ እንዲችሉ ተጨማሪ መረጃዋችን ይጠባበቁ።

ተጨማሪ መረጃ በዚህ ያግኙ፤ superintendent’s reopening update presentation (PDF) ለትምህርት ቤት ቦርድ በጃንዋሪ 7 የሰጡት ምላሽ።

## በካፒቶል እሮብ ቀን ስለተከሰተው ሁኔታ ከልጆችዋ ጋር ለማውራት የሚያግዙ ድጋፍ ሰጪ ነገሮች ሪሶዋርሶች



በካፒቶል እሮብ ቀን በዲ.ሲ ከተማ የተከሰተውን አመፅ በተመለከተ የእኛ ተማሪዎች የማህበራዊ እና የስሜት የተጠበቀ እንዲሆን ለማረጋገጥ የእኛ አስተማሪዎችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ግዚያቸውን በመውሰድ ተዘጋጅተዋል።

ከዚህ በታች የቀረቡት በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ድጋፍ ሰጪ የሚሆኑ ሪሶዋርሶች ናቸው ። ሁላችንም ምን እንደተፈጠራ ለመረዳት እየጣርን እንገኛለን።

[Education Week: Caring for Students in the Wake of a Tragic News Event]

[Common Sense Media: How to Talk to Kids About Violence, Crime, and War]

[Teaching Tolerance: When Bad Things Happen (Toolkit)]

[ASCA: Helping Students in Troubling Times]

## የተለመዱ የክትባት ማስታወሻዎች



ተማሪዎቻችን ወደ ት/ቤት ለመቀበል በምንዘጋጅበት ወቅት እባክዎን ልጅዎ ወቅታዊ በየክፍል ድረጃ የሚሰጡ ክትባቶችን ማሟላታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ። ይህን ይመልከቱ፤ Virginia Department of Health's Immunization Requirements.

ለልጆች የክትባት ለማግኘት ያሉ አማራጮች፤

- Neighborhood Health
  ባዙ ቦታዎች ፤ የህክምና ፣ የጥርስ እና የአእምሮ ጤና አገልግሎት በዝቅተኛ ዋጋ እንዲገቢ መጠን ይሰጣል።
- የወጣቶች ጤንነት ማእከል በቲ.ሲ. ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ የኪንግ ስትሪት ግቢ ተማሪዎች አገልግሎት ይሰጣል። ሌሎች አገልግሎቶች ለተማሪዎች እድሚያቸው ከ12 እና በላይ ለሆኑ ይሰጣል። አገልግሎት በገቢ መጠን እየታየ በክፍያ ይሰጣል።
- የእርስዎ ተማሪው የልጆች ሐኪም

## አዲስ ዙር በወረርሽኝ ምክንያት የሚሰጡ ኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ በቅርብ ይጀመራል

መልካም ዜና! የፌደራል መንግስት አዲስ ዙር በወረርሽኝ ምክንያት የሚሰጡ ኤሌክትሮኒክ የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ በቅርብ ይጀመራል (P-EBT)

ሁሉም P-EBT ብቁ የሆነ እያንዳንዱ ቤተሰብ እንዴት ማመልከት እንደሚችል እርግጠኛ መሆን እንፈልጋለን። እናም በዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምግብ መግዣ የSNAP በሚቀበሉ ማንኛውም ቦታ የሚያገለግል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።

- **ካርድ አለዎት?** በኦክቶበር 2020 P-EBT ተጠቃሚ ሆነው ከነበረ ምንም ማድረግ አይጠበቅምዎትም። በተጨማሪ ገንዘብ ባለዎት ካርድ ላይ ይጨመራል።
- **ካርዱ ጠፍቶል?** ለመተካት በስልክ ቁጥር -866-281-2448 ይደውሉ። እባክዎን ያስታውሱ፤ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ካርድ አያከፋፍልም።

- **በነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ ለማግኘት ከሴፐቴምበር 21፣ 2020 በሆላ አመልክተዋል?** በነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ ለማግኘት ከሴፐቴምበር 21፣ 2020 ማመልከቻ **በሆላ** ከሞሉ እና ማመልካቻው መድረሱ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከተቀበሉ ከካርዱ በቅርብ ግዜ ሊደርስዎ ይችላል። ምንም ተጨማሪ ስራ ማድረግ አያስፈልግም።
- **ሁኔታዋች ተቀያይረዋል?** የስራ / ገንዘብ ሁኔታ ከተለወጠ ወይም ከሴፐቴምበር 21 ፣ 2020 ወደ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከመጡ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ይችላሉ። የ P-EBT ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ ስለመሆንዎ ለማወቅ የነፃና በአነስተኛ ክፍያ ምግብ አቅርቦት ማመልከቻ መሙላት ይኖርብዋታል። እባክዎን [ማመከታችው በኦንላይን ይሙሉ](#) ከጃንዋሪ 13, 2021 በፊት ወይም የወረቅት ማመልካቻ ቅፁን ከምግብ ማከፋፈያ ቦታዋች በአንዱ ማግኘት ይችላሉ። ቅፁን በፓስታ ቤት ወይም በምግብ ማከፋፈያ ቦታ ላሉ ሰራተኞች እስከ ጃንዋሪ 13 ፣ 2021 ድረስ መስጠት ይችላሉ። ቅፁብ ለመሙላት እርድታ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን በዚህ ግንኙነት ይድርጉ። [Virtual PLUS+ Helpline](#).
- **ተጠቃሚ ሊሆን የሚችል ሰው ያውቃሉ?** ተጠቃሚ ሊሆን የሚችል ቤተሰብ የሚያውቁ ከሆነ መልክቱን በማዳረስ እገዛ ያድርጉ።

መልሶ እዚህ ይመልከቱ [ስለP-EBT በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዋች](#).

## የቴ.ሲ እና የማውሪ አዲስ ስም ስያሜ ለተማሪዋች የመጨረሻ እድል




ዛሬ የመጨረሻው ቀን ነው ለተማሪዋች አንድ ፅሁፍ ወይም ፓስተር ለማዘጋጀት አዲስ ስያሜ የቲ.ሲ. ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ማቲው ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በተመለከተ። [Learn more about this process](#).

በሚቀጥለው ሳምንት በተማሪዋች የቀረቡ ስያሜዋች በሚመለከት የኮሚዮኒቲ አባል እና ሰራተኞች ያላቸውን ምርጫ እንዲገልፁ እንዲሁም ተጨማሪ ስያሜ ለማቅረብ ኮሚዩኒቲ አስተያየት ማሰባሰቢያ ዝግጅት ይኖራል።

**[VIDEO: The Process of Choosing New Names for T.C. and Maury](#)**

## የትምህርት ቤት ቦርድ Alderton በ2021 በሊቀመንበርነት ለመሾም ውሳኔ ሰጠ።



የኤሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ Meagan L. Alderton የቦርዱ ሊቀመንበር እንዲሁም Veronica R. Nolan በዚህ ዓመት ምክትል ሊቀመንበርነት መርጦል።

በአሌካሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ታሪክ Alderton በመጀመሪያ የዲስትሪክት C በመወከል በትምህርት ቤት ቦርድ በኖቬምበር 2018 የተመረጡ ሲሆን አፍሪካ አማሪካዊ ቦርድ ሊቀመንበርት ተመራጭ በመሆን ሁለተኛው ሴት ናቸው። እርሳቸው የመጀመሪያዎ አፍሪካ አሜሪከዊ ሴት የቦርድ ሊቀመንበር በመሆን 1980-82 ድረስ ባገለግሉት Shirley Tyle እግር ተተከተው የሚያገልግሉ ናቸው። Tyler ከFerdinand T. Day በመቀራረብ አብረው ሰርተዋል። ከFerdinand T. Day በ1964 የመጀመሪያው የአፍሪካ አሜሪካዊ በጀርጅኒያ ስቴት ቦታ በመያዝ ያገለገሉ ናቸው— ከ Brown versus Board of Education decision- ውሳኔ 10 ዓመት በኋላ የሆነ ነው።

ተጨማሪ ለማንበብ፤.

## ሱፐር ኢንቴንደንት የጥምር ፈንድ የስራ ማስኬጃ በጀት ለመልሶ ግንባታ፣ ሰራተኞችን በስራ የማቆየትና የማጠናከር ስራ የሚያግዝ በጀት ራቂቅ አቀረቡ።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሱፐር ኢንቴንደንት ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr.) ሱፐር ኢንቴንደንት የጥምር ፈንድ የስራ ማስኬጃ FY22 በጀት ዓመት በጀት ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመልሶ ለማገመም የሚያስችል ፣ ከዘር መድልዎ ጋር በየተያያዘ የማጥናከር ስራ የሚያግዝ በጀት ራቂቅ አቀረቡ

የጥምር በጀት $320.59 ሚሊዪን ሲሆን የትምህርት አሰጣት ፕሮግራሙን የሚያግዝ የባከነው የትምህርት ሂደት የሚያዝ ፣ ጥራት ያለው ሰራተኞች የመመልመልና የማቆየት ሂደት እና የማስተማር፣ የመማር  ፍቅርን የአመራር ስራ የሚያሳድግ ይሆናል።  በተጨማሪ አጠቃላይ የገንዘብ አመዳደብ የዲቪዝኑ ስራ የዘር እኩልነት ዋነኛው ጉዳይ ላይ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚያግዝ ይሆናል።

የበለጠ ለማንበብ ይህን ይመልከቱ፤  the proposed budget.

## ቦርዱ ተገቢ ኋላፊነት አጠቃቀም የሚያሳይ የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት አፀደቀ።

የኤሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ የ10 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም( CIP)  በጀት አፀደቀ  አሁን ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ያገናዘበ  ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ህንፃዋቹ እና ቴክኒዋሎጂዋችን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችለው  በጀት አፅድቆል።

የፀደቀው የ2022-2031 CIP በጀት  ድምር $551483,000  ሲሆን የቴክኒዋሎጂ መሻሻል ለማድረግ ፣ ኦንላይን እና የወረቀት መፅሃፍት ለመግዛት እና የቴ.ሲ.  ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚኒ ሐዋርድ ግቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት  የማስፋፋት ፕሮጀክት ያገለግላል።  ይህም ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በፖርጋም እቅድ መሰረት የተማሪ የመቀብል አቅም በማሳደግ እገዛ ያደረጋል በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲሁም ትምህርት ቤት በቴክኒዋሎጂ ወቅቱን የተጠበቁ እንዲሆን ያስቻላል።

የትምህርት ቤት ቦርዱ ያፀደቀው በጀት የአስቸኳይ የህንፃ ጥገና እንደ HVAC ፣ የጣራ ፣ የደህንነት እና ጥበቃ እገዛ ያደርጋል።  ሆኖም ግን የጆርጅ ሜሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና የኮራ ኬሊ አንደኛ ደረጃ የሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኒዋሎጂ ት/ቤት በአንድ ዓመት እንዲዘገይ ተደርጎል አሁን ባለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ምክንያት።  የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትራንስፓርት ተቆማት ማሻሻል በተጨማሪ በአንድ ዓመት እንዲራዘም ተደርጎል። እና አዲስ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤት እና የማቲው ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ማሻሻል በሁለት ዓመት እንዲራዘም ተወስኖል።

Read more about the ACPS Strategic Plan:

## ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.  የተቆማት አደረጃጀትና አመራር አዲስ ስራ እስፈፃሚ ሾመ።



ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የዶ/ር. Alicia Hart  ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.  የተቆማት አደረጃጀትና አመራር አዲስ ስራ እስፈፃሚ በመሆን ተሹሙ መሆኑን በደስታ ይገልፃል።

የዶ/ር. Alicia Hart  ከዲሴምበር 2019 ጀምሮ ወደ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በትምህርት ተቆማት ዳይሬከተርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ስለ የዶ/ር. Alicia Hart ተጨማሪ መረጃ፤Read more about Dr. Hart.

## የምግብ አቅርቦት

ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎችና እድሚያቸው ከሁለት አመት በላይ ለሆኑ ልጆች የምግብ አቅርቦት ብዙ የማከፋፈያ ቦታዎች በመላው አሌክሳንደሪያ ከተማ አሉት። የምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች የሚያሳየው ከካርታ ይመልከቱ .

**ይዞ-መሄድ የምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች:**

ይዞ-መሄድ ቁርስ፣ ምሣ እና መክሰስ (ስናክ) ምግቦች ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ከጥዋት 7.30 እስከ ከቀኑ 12.00 ድረስ በሚከተሉት ቦታዎች ይሰጣል፤

- **ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት**
  5700 Sanger Avenue Alexandria, VA 22311
- **የፍራንሲስ ሲ ሐመንድ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**
  4646 Seminary Road, Alexandria, VA 22304
- **ኮራ ኬሊ አንደኛ ደረጃ የሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኒዋሎጂ ት/ቤት፤**
  3600 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305
- ጀፈርሰን ሁዊስተን ቅደመ-መደበኛ - 8ኛ IB ትምህርት ቤት
  1501 Cameron Street, Alexandria, VA 22314
- **ማውንት ቨርነን የኮሚዩኒቲ ት/ቤት**
  2601 Commonwealth Avenue, Alexandria, VA 22305
- **ፓትሪክ ሔንሪ K-8 ት/ቤት**
  4643 Taney Avenue, Alexandria, VA 22304
- **የቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት**
  3330 King Street Alexandria, VA 22304

እንዲሁም ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት በ "ተንቀሳቃሽ - ፓፐ አፕ" የማከፋፈያ ቦታዎች የሚገኙበት ቦታዎች፤

- **ሜሶን አፓርትሜንት (Mason Apartments)** በ **South Reynolds Street Alexandria, VA 22304**10:45 እስከ 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት ።
- **ብረንት ፕሌስ አፓርትሜንት (Brent Place Apartments)** በ **375 South Reynolds Street, Alexandria, VA 22304** 11:20- 11:50 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ
- **ሩቢ ተከር የቤተሰብ ማእከል (Ruby Tucker Family Center)** በ **322 Tancil Court, Alexandria**, VA 22314 10:45 - 11:15 ጥዋት ሰኞ ፣ እሮብ እና አርብ
- **ኮሚዮኒቲ ሎጂንግ (Community Lodgings)** በ **607 Notabene Drive, Alexandria, VA 22305** ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።
- **አልድ ታወኒ ዌስት አፓርትሜንት (Old Towne West Apartments)** (የመኪና ማቆሚያ ቦታ) በ 500 South Alfred Street, Alexandria, VA 22314
  ጥዋት 11:20 - 11:50ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።
- **ፎሎረንስ ድራይቭ እና ፎር ማይል መገናኛ መንገድ(Florence Drive** እና **Four Mile Road**) **Alexandria, VA 22305** ከጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት።
- **ዘ ፊልድስ** (**The Fields)** በ **4309 Duke Street, Alexandria, VA 22304** ጥዋት 10:45 - 11:15 ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ።

- **በቤንጊተን ክሮኒሲንግ (Bennington Crossing) አፓርትሜንት በ 441 North Armistead Street, Alexandria, VA 22312** ጥዋት 11:30 እስከ እኩለቀን ድረስ ሰኞ፣ እሮብ እና አርብ ቀናት ።
- **(ከባንክ ኦፍ አሜሪካ ጀርባ) 2727 Duke Street , Alexandria, VA 22314** 10:45 እስከ 11:15 ጥዎት

**ምግብ ለማግኘት ምዝገባም ሆነ ስም መፃፍ አያስፈልግም።**

**<u>ማስታወሻ፤</u> ማክሰኞ እና ሐሙስ ምንም የምግብ ክፍፍል አይኖርም።** የተወሰኑ ቀናት እንዲሆን መደረጉ የሶሻል መራራቅን አሰራር ለመከተል እና አስፈላጊ ያልሆኑ ግንኙነቶችን ለመቀነስ ነው። ለሁለት ቀናት የሚሆን ምግብ ሰኞ እና እሮብ ቀናት ይከፋፈላል እንዲሁም አርብ ለሶስት ቀናት የሚሆን ምግብ ይሰጣል።

**የአሌክሳንደሪያ ከተማ ሌሎች የምግብ አቅርቦት ምንጮች**

በአሌክሳንደሪያ ከተማ የምግብ ማቅረቢያ በታዎች እና ሰዓት የጊዜ ሰሌዳ ለማወቅ ይህን ይመልከቱ።
[www.hungerfreealexandria.com](http://www.hungerfreealexandria.com) ወይም ስልክ 703-662-1067. .

**ጥያቄዎች? ወይም አስተርጎሚ ይፈልጋሉ?**

ጥያቄዎን በስፓኒሽ፣ በአረብኛ ወይም በአማርኛ ቴክስት ያድርጉ፤
- ACPSMEALS to 797979 (እንግሊዘኛ እና ስፖኒሽ፤)
- ለ703-927-6866 ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ (በአማርኛ )
- ለ703-927-7095 ይደውሉ ወይም ቴክስት ያድርጉ (በአረብኛ )

ወይም

የኤፍ.ኤ.ሲ.ኢ.(FACE) ማእከል የጥምር ቋንቋ ተናጋሪ የወላጆች የመረጃ መስመር አሁን ከሰኞ - አርብ ከጥዋት 9.00 እስከ 1.00 ቀን ድረስ ይኖራል።
- የስፓኒሽ/እንግሊዘኛ 571-775-9719 ስልክ ይደውሉ።
- የአማርኛ/እንግሊዘኛ 703-927-6866 ስልክ ይደውሉ።
- የአረብኛ/እንግሊዘኛ 703-927-7095 ስልክ ይደውሉ።

**የደህነት ማስታወሻ**

እባክዎን ያሳታውሱ በእርስዎ እና በሚቀጥለው ቤተሰብ ወይም ሰዎች መካከል በምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች ስድስት ፊት ርቀት በመጠበቅ የሶሾል ዲስታንሲንግ (ተራርቆ መቆም) አሰራር ያክብሩ።

ማንኛውም የመተንፈሻ አካላት ህመም ምልክቶች ያሉት ሰው ለምሳሌ ትኩሳት፣ አፍንጫ መዝረክረክ፣ የሚከረከር ጎሮሮ ፣ ሳል፣ ወይም የመተንፈስ ችግር የምግብ ክፍፍል በሚደረግበት ቀን ወይም ከዚያ ቀን 24 ሰዓት በፊት ከለብዋት እባካችሁ ወደ ምግብ ማከፋፈያ ቦታ አይምጡ። እና ወደ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ይደውሉ። የራስዎ ሐኪም ከሌለዋት እና በክሊኒክ ያልተመዘገቡ ከሆነ የአስቸኳይ ጊዜ ህክምና ወይም የድንገተኛ ጊዜ ህክምና ቦታ ይደውሉ።

## ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ወቅታዊ መረጃ

ለማንኛውም ወቅታዊ መረጃ ይህን ይመልከቱ፤ [www.alexandriava.gov/Coronavirus](http://www.alexandriava.gov/Coronavirus).

# የጤና ጉዳይ ማሳሰቢያዎች

**ጤንነት አይሰማዎትም?**

ከቤተሰብ ሀኪም ጋር ይገናኙ፤ ምንም የጤና ኢንሹራንስ የለዎትም? ከኔበርሁድ ሄልዝ(Neighborhood Health) ጋር  በስልክ ይገናኙ 703-535-5568.

---

**ጥያቄዎች፣ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም አስተያየት ? ከእኛ ጋር ይገናኙ፤.**